የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱____
አዲስ አበባ ህዳር ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28 th Year No. 39
ADDIS ABABA 15th November, 2019_____

ማውጫ

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ

ቁጥር ፩፻፲፭/፪ሺ፲፪

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የካቢኔ ደንብ

ገፅ----------፪ሺ፻፳

<u>የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ</u>

<u>ቁጥር ፩፻፲፭/፪ሺ፲፪</u>

<u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የካቢኔ ደንብ</u>

በከተማው እያደገ የመጣውን የቤትና ሌሎች ሲቪል ስራ ግንባታዎች አስተማማኝ ለማድረግ፣ ፈጣን እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማምጣት፣ ድህነትን ለመቀነስ፣ የቤት ግንባታና ተጓዳኝ ችግሮችን መቅረፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማ አስተዳደሩ የሚገነቡ ቤቶችና ከቤት ጋር ተያያዥ የሆኑ ግንባታዎችን በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋና በተቀመጠለት ጊዜ በመገንባት እያደገ የመጣውን የህዝብ ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥና በራሱ ገቢ የሚተዳደር የከተማው አስተዳደር የግንባታ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም በማስፈለጉ፤

CONTENT

ያንዱ ዋጋ 2.80
Unit price

a city Cabinet Regulation No. 115/2019

A Regulation To Provide For The Establishment Of The Addis Ababa City Government Construction Enterprise

Page----------2120

<u>ADDIS ABABA CITY CABINET REGULATION NO. 115/2019</u>

<u>A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT CONSTRUCTION ENTERPRISE</u>

WHEREAS, it has found necessary to make the increasing construction of houses and other civil works in the city reliable; to ensure fast and sustainable economic development; to reduce poverty; to alleviate housing construction and other related problems;

WHEREAS, it has found necessary to establish a construction enterprise of the City Government that runs its business by its own and carry out the construction of quality, economic and timely houses and housing related constructions executed by the City Government so as to address the increa[illegible]r the there[illegible]

፪ሺ፻፳፩
አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፱፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፤ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፰፱/2ሺ፲1 እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፸፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና አንቀጽ ፺፭ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የካቢኔ ደንብ ቁጥር ፩፻፲፭/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

. <u>መቋቋም</u>

፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ኢንተርፕራይዝ (ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዝ" እየተባለ የሚጠራ) የከተማው አስተዳደር የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪.የኢንተርፕራይዙ ተጠሪነት ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፤

፫.ኢንተርፕራይዙ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን እና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፩ መሰረት ይተዳደራል።

፫. <u>ዓላማዎች</u>

ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የሥራ ተቋራጭ ሆኖ ቤትና ከቤት ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የግንባታ፣ የዲዛይን እና መሰረተ ልማት ስራዎችን መስራት፤
2. የግንባታ መሳሪያዎችንና ማሽነሪዎችን ማከራየት፣ የ ግብአት ማምረት እና መሸጥ፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-article 3 of Article 61 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Re-establishment and to Promlugate the power and duties of the thereof Proclamation No. 64/2019 and the power vested as per Article 95, the Addis Ababa City Cabinet has issued this Regulation as follows.

1. Short Title

This Regulation may be cited as: "The Addis Ababa City Government Construction Enterprise Establishment Regulation No. 115/2019."

2. Establishment

1. The Addis Ababa City Government Construction Enterprise (hereinafter the **"Enterprise"**) is hereby established as a public enterprise of the City Government by this Regulation.
2. The Enterprise shall be accountable to the Housing Development and Administration Bureau of the City.
3. The Enterprise shall be governed by Regulation No. 14/1998 which provides for the administration of public enterprises of the Addis Ababa City Government and the establishment of the thereof.

3. Objectives

The following are the establishment objectives of the Enterprise:

1. Carry out housing and housing development related constructions, designs and infrastructural works as a contractor;
2. Lease construction materials and machineries; produce construction inputs and sell the thereof;

፫. የቤትና ተያያዥ የግንባታ ስራዎችን ለማስፋፋት ከሀገር ውስጥና ከውጭ አቻ ተቋማት ጋር አግባብነት ባለው ሕግ ግንኙነት በመመስረት የግንባታ ስራውን ማከናወን፣

፬. ለኢንተርፕራይዙ ልማትና እድገት የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው አይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የምርምር፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በውድድር መንፈስ እንዲሰራ ማስቻል፤

፭. በቤት ግንባታና ተጓዳኝ የግንባታ ዘርፉ ስራዎች የሚታዩትን የግንባታ የማስፈጸም አቅምና የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ክፍተቶችን መሙላት፤

፮. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን ማካሄድ።

፬. ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የኢንተርፕራይዙ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል።

፭. ዋና መስሪያ ቤት

የኢንተርፕራይዙ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ቦታ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፮. ካፒታል

ለኢንተርፕራይዙ የተፈቀደው ጠቅላላ ካፒታል ፫ ቢሊዮን ብር (ሶስት ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 648,050,158.72 (ስድስት መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን አምሳ ሺህ አንድ መቶ ሀምሳ ስምንት ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም) በጥሬ ገንዘብና ብር 101,949,841.27 (አንድ መቶ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ

አርባ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) በዓይነት ተከፍሏል።

3. Carry out construction works through establishing relations, as per the law, with equivalent local and foreign institutions so as to expand housing and housing related construction works;
4. Strive towards working in a competitive manner with the concerned research, educational and training institutions so as to produce the required trained manpower in type, number and quality for the development and growth of the enterprise;
5. Address construction execution capacity and technology utilization gaps which exist in the housing construction and related construction sector works;
6. Carry out other related activities so as to attain its objectives.

4. Monitoring Authority

The Addis Ababa City Government Public Enterprise Monitoring Authority shall be the monitoring authority of the Enterprise.

5. Head Office

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices at any place, as may be necessary.

6. Capital

The authorized capital for the Enterprise is birr 3,000,000,000.00 (three billion birr); of which birr 648,050,158.72 (six hundered fourty eight million fifty thousand one hundered fifty eight birr and seventy two cents) is paid up in cash and 101,949,841.27 (one hundered one million nine hundered fourty nine thousand eight hundered fourty one ፪ሺ፱፻፹፫ r and twenty seven cents) in kind.

፯. ኃላፊነት

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. ኢንተርፕራይዙ የሚቆይበት ጊዜ

ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

፱. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፺፱/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) የተቋቋመው የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የማምረቻ ማዕከላት በዚህ ደንብ ለግንባታ ኢንተርፕራይዙ ተላልፏል።

፲. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከህዳር 6 ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር 6 ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

Deputy Mayor of the Addis Ababa City

7. Liability

The Enterprise shall not be liable beyond its total asset.

8. Duration of the Enterprise

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. Transfer of Rights and Obligations

The Rights and Obligations of the Housing Development Corporation manufacturing centers established under Proclamation No. 64/2019 are hereby transferred to the Construction Enterprise by this Regulation.

10. Effective Date

This Regulation shall enter into force as of 15th November, 2019.

Done at Addis Ababa, this 15th day of November, 2019

Takelle Umma Banti